| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ሐተታ ፡ መጻሕፍት ። |
| ርእስ ፤ | መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ። (2) |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ሐተታ ፡ መጻሕፍት ።

## Books Review | revue de livres



ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ከባልተቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ እታገኘኹ ፡ ባዬ ፡ እና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋራ ፥ በከፊል ፤ ጂግጂጋ ፥ 1922 ፡ ዓ.ም. ።

በቅርቡ ፡ ከደረሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፥ የሚከተሉት ፡ የብላታ ፡ መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ (1891-1923 ፡ ዓ.ም.) ፡ መጻሕፍት ፡ በቁም ፡ ነገራቸው ፡ ይጠቀሳሉ ፦

- **መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ** ፤ *"ትዝታዬ ፤ ስለ ፡ ራሴ ፡ የማስታውሰው ፤ 1891-1923 ፡ ዓ.ም. ። "* ፡ በአምኃ ፡ መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ የተዘጋጀ ፤ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፤ 252 ፡ ገጾች ። ISBN 978-0-578-02223-9 ።




- **መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ** ፤ *"ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ 1922-1927 ፡ ዓ.ም. ። "* ፡ በአምኃ ፡ መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ የተዘጋጀ ፤ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ምድራስ ፥ 2009 ፡ ዓ.ም. ፤ 261 ፡ ገጾች ። ISBN 978-99944-52-75-C ።




ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ (1891-1971 ፡ ዓ.ም.) ፥ ከወጣትነታቸው ፡ ዠምሮ ፥ ካገር ፡ አስተዳደር ፡ ጋራ ፡ በቀለም ፡ መስክ ፡ ባሳዩት ፡ ችሎታና ፡ ባበረከቱት ፡ የላቀ ፡ አገልግሎት ፥ ከእንኅኑይ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፣ ከእንማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ጋራ ፡ የብላታነት ፡ ማዕርግን ፡ ያገኙ ፡ ታላቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቅ ፡ ናቸው ።

ቀደም ፡ ሲል ፡ ታትመው ፡ ካነበብናቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ሌላ ፥ በርከት ፡ ያሉ ፡ ገና ፡ ያልታተሙ ፡ መኖራቸው ፡ ይሰማ ፡ ነበር ። ዛሬ ፥ ልጃቸው ፡ አቶ ፡ አምኃ ፡ መርስዔ ፡ ሐዘን ፥ እጅግ ፡ በሚያስመሰግን ፡ ጥንቃቄና ፡ ጥራት ፡ ካሳተማቸው ፡ ጥቂቶቹ ፡ ውስጥ ፡ እነዚህ ፡ የዘመናዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ መዛግብት ፡ ይገኙበታል ። በጠቅላላው ፥ አጻጻፉ ፡ የታረመ ፥ ትረካው ፡ የተረገጠ ፣ ባገር ፡ ፍቅር ፡ መንፈስ ፡ የከበረ ፣ በጨዋነት ፡ ለዛ ፡ የተነገረ ፣ በትኽክለኛና ፡ በብርቅ ፡ መረጃ ፡ የተሞላ ፡ አስደሳች ፡ ንባብ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፥ እንዲሁም ፡ የወቅቱን ፡ ኹኔታ ፡ የሚመረምሩ ፡ ኹሉ ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ ቀድመው ፡ ሊያነቧቸውና ፡ ሊያጠኗቸው ፡ ይገባል ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።